# እባክህ ተወን በቀቀን!




ልማድ ሆኖብህ ማቀንቀን ተፈጥሮህ ሆኖ ማሰማት ገደል ማሚቱን፣
እኩይ ፈልስጣ ተወንበሩ ላይ ጉብ ብሎ መፍትሔው አንድና አንድ ነው ሲሰብከን፣
አንተም ቀበል አድርገህ ትርጉም የሌለው አንድና አንድ ነው አፏጨህብን።

ትንሽ ቆይቶ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ብሎ እንደ ቃልቻ ሲያጎራ ሲደነፋብን፣
አንተም ህዳሴና ቦንድ ጨፍረህ ተወዲያ ወዲህ ዘጥ! ዘጥ! አልክብን።

ከዓመታት በፊት ቀበሮ የበግ ለምድ ለብሶ መደመር እያለ ሲሰብከን፣
ላንቃህ ሰማይ እስተሚነካ ቦርግደህ እንደ መብረቅም አጉልተህ ድምጥህን፣
መደመር ብለህ እየወሸከትክ ጆሯችን መግል እስከሚቋጥር ጮህክብን።

ተዚያም ቀጥሎ ጁንታ መጣልህ እያለ ጧት ማታ ሲያንባርቅብን፣
ጁንታ! ጁንታ! እያልክ እንደ ዶሮ ማነቂያ ሰካራም ቀባጠርክብን።

ጁንታ ታለው ጋር ግብረ ሰዶምን ፈጥሞ ጃውሳ ወረረህ ሲሰብከን፣
የጃውሳ ተረት ያለ ምንተ እፍረት እንደ ዝሐ ክር ተረተርክብን።

አፍ እየጠበክ ያለ እረፈት መቀባጠሩ የማይሰለችህህ በቀቀን፣
ሳጥናኤል ነገ ሌሊትም አቃዥቶት እንደ ልማዱ በሕዝብ ሲተፋ ምራቁን፣
ተምላሱ ላይ እንደ ጭልሌ ሞጭለፍ አድርገህ ምን ትለን ይሆን?

እባክህ ንስህ ግባ ይብቃህ! ተሰይጣን ላንቃ ላፍ እያረክ መድገሙን፣
በፍጥረት አምላክ ተለመን! እባክህ ተወን! ተወን! በቀቀን!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ነሐሴ ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓ.ም.